Maahanmuuttovirasto
Migrationsverket
Finnish Immigration Service

# ለፊንላንድ የኮታ ስደተኛ ምርጫ

**ይህ መመሪያ በጦርነት፣ በስደት ወይም በግጭት ምክንያት ከትውልድ አገራችሁ ወደ ሌላ ሀገር ለተሰደዳችሁ፣ በUNHCR ባለ ጉዳይ ሆናችሁ ለተመዘገባችሁ እና ለዓለም አቀፍ ጥበቃ ላመለከታ ችሁ የተዘጋጀ ነው።**

## 1. የዩ.ኤን.ኤች.ሲ.አር (UNHCR) አቅርቦት ለፊንላንድ



ለተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ኤጀንሲ ዩ.ኤን.ኤች.ሲ.አር ሰራተኞች ለስደተኛነት ያበቃዎትን ምክንያቶች እና በቤትዎ እና በትውልድ ሃገርዎ ውስጥ ስላለው ሁኔታ ነግረዋቸዋል። **ዩ.ኤን.ኤች.ሲ.አር** የመልሶ ማቋቋሚያ እንደሚያስፈልግዎ ተመልክቷል። ዩ.ኤን.ኤች.ሲ.አር ለዬትኛው አገር የመልሶ ማቋቋም ጥያቄ ሊያቀርብልዎ እንደሚገባ መምረጥ አይችሉም፣ እዲሁም ፊንላንድ የተወሰኑ የኮታ ስደተኞች ብቻ ወደ ፊንላንድ እንዲቀርቡ አትጠይቅም።.

ዩ.ኤን.ኤች.ሲ.አር በፊንላንድ ውስጥ እንዲሰፍሩ መተዋውቅያ ለማቅረብ ወስኗል። ዩ.ኤን.ኤች.ሲ.አር ለፊንላንድ የስደተኞች አገልግሎት ስለ ማንነትዎ እና ሁኔታዎ በመረጃ የታገዘ ገለጻ አቅርቧል።

## 2. የኮታ ምርጫ ቃለ መጠይቅ



ፊንላንድ ዩ.ኤን.ኤች.ሲ.አር ያቀረበዉን ማስተዋወቅያ አስተናግዳ ቃለ መጠይቅ ታደርግሎታለች። የኮታ ምርጫ ቃለ መጠይቁ የሚከናወነው በሚኖሩበት ሀገር፣ ወይም ከፊንላንድ ርቀው ባሉበት ሀገር ነው።.
የፊንላንድ መራጭ ልዑካን ከተለያዩ ድርጅቶች የተውጣጡ ኃላፊዎች አሉት። መራጭ ልዑካኑ ለስደተኝነትዎ ምክንያት የሆኑትን ሁኔታዎች እንዲሁም በትውልድ እና በሚኖሩበት ሀገር ስላለው ሁኔታ ተጨማሪ ጥያቄዎችን ይጠይቅዎታል። በቃለ መጠይቁ መልሶ ማቋቋም ለእርስዎ የተሻለ መፍትሄ ይሆን እንደሆነ ያረጋግጣል። ያቀረቡት መረጃ መረጃውን የማግኘት መብት ባላቸው የፊንላንድ ባለስልጣናት ይከናወናል። መረጃዎ በአገርዎ ላሉ ባለስልጣናት አይሰጥም።
ስለቤተሰብ ዳግም ውህደት እና ስለግል መረጃዎ ሂደት በቃለ መጠይቁ ቀን፣ መመሪያዎች ይደርስዎታል።

## 3. የ ኢሚግሬሽን ጽ/ቤት ዉሳኔ



የኮታ ምርጫ ቃለ መጠይቅ ከተደረገ ከሁለት ወራት በኋላ የፊንላንድ የኢሚግሬሽን አገልግሎት የምርጫ ውሳኔ ይሰጣል
የፊንላንድን የምርጫ ውሳኔ መረጃ ከማግኘትዎ በፊት የራስዎ ወይም የቤተሰብዎ ሁኔታ ከተቀየረ ስለ ተከሰተው ለዉጥ መረጃ ለ ዑኘሕጬር ያቅርቡ። እንደነዚህ ያሉ ለውጦች ለምሳሌ አዲስ ጋብቻ፣ እርግዝና ወይም የግንኙነት ለውጥ፣ አዲስ መረጃ ሊሆኑ ይችላሉ።

Maahanmuuttovirasto
Migrationsverket
Finnish Immigration Service



## 4. የመኖሪያ ፈቃድ መስጠት

በፊንላንድ የስደተኞች ኮታ ውስጥ ከተመረጡ፣ የኢሚግሬሽን ቢሮ የመኖሪያ ፈቃድ ይሰጥዎታል። የውሳኔዎ መረጃ ከአንድ የዩ.ኤን.ኤች.ሲ.አር የስራ ባልደረባ ይደርሰዎታል።

## 5. ስልጠና ስለ ፊንላንድ ማህበረሰብ



በሚኖሩት ሀገር ከ3 -4 ቀን የሚቆይ የረጅም ጊዜ ስልጠና ልናዘጋጅልዎ ዓላማ ያለን ሲሆን፣ ወደ ፊንላንድ ስለመዘዋወር፣ ስለፊንላንድ ማህበረሰብ እና የፊንሽ ቋንቋ ስለመማር መረጃ ይሰጥዎታል። ስልጠናው የሚደራጀው በአስተርጓሚ ወይም በአፍ መፍቻ ቋንቋዎ ነው። የዓለም አቀፍ የስደተኞች ድርጅት IOM የስልጠናውን ቀን እና ከስልጠናው ጋር የተያያዙ ፖሊሲዎችን ያሳውቅዎታል። በስልጠናው ወቅት ፊንላንድ ለስልጠናዎ እና ለጥገናዎ ይከፍላል።

.

## 6. ወደ ፊንላንድ ስለመዛወር



የፊንላንድ ባለስልጣናት በፊንላንድ ውስጥ እርስዎን የሚቀበል ክልለሰብ ያዘጋጅልዎታል። ከመኖራያ ክልለሰቡ የተለያዩ አገልግሎቶችን ፣ ለምሳሌ ትምህርትን፣ ሥራን፣ ማህበራዊ እና የጤና አገልግሎቶችን፣ እና የልጆች መዋእለ ሕጻናት፣ ትምህርት ቤትን የመኖራይ ቤት ድጋፍ፣ እንዲሁም መመሪያ እና ምክር ያገኛሉ።

የሚቀበልዎ ክልለሰብ የመኖርያ ቤት አዘጋጅቶሎት ሲያበቃ አይ ኦ ዔም በፊንላንድ የስደተኛ አገልግሎት ጥያቄ መሰረት ወደ ፊንላንድ የሚያረጉትን ጉዞ ያደራጃል እና ለመጓዝ አስፈላጊ ሰነዶችንም ይቀበላል። አይ ኦ ኤም ከርስዎ ጋር ግንኙነት ያደርግና ተግባራዊ የጉዞ ዝግጅቶች መሙዋልታቸውን ያረጋግጣል። የፊንላንድ ኢሚግሬሽን አገልግሎት ከሚኖሩበት ሀገር ወደ ፊንላንድ ለሚያደርጉት ጉዞ ወጪውን ይከፍላል።

የፊንላንድ ቀይ መስቀል (አስ.ጸ.ዓር) በፊንላንድ በሚገኘው በሄልሲንኪ-ቫንታ አውሮፕላን ማረፊያ ይቀበልዎታል። ከአየር ማረፊያው፣ ጉዞዎ ይቀጥላልና ወደ ግልዎ ክለለሰብ በመጓዝ አዲሱ ቤትዎ ይደርሳሉ።

## ተጨማሪ መረጃ :

መረጃ
ስለ ስለግል ማስረጃ አያያዝ:
link.migri.fi/
henkilotietojen-kasittely-am

መርጃ
ስለ ቤተሰብ ዳግም ዉህደት :
link.migri.fi/
perheenyhdistaminen-am